

ሁሌም የምንወደው እና የምናከብረው ከልባችን የማይጠፋው ሰለሞን አፅብሃ ባልታሰበ እና ባልተጠበቀ ሁኔታ November 30, 2019 ከዚህች አለም ተለይቶናል። ከሁሉም የበለጠ ሰላም እና ደስተኛ በነበረበት ሰአት ማንም እንዲ ይሆናል ብሎ ባልጠበቀበት ሰአት ጓደኞቹን አልጋው ላይ ጋደም ብሎ በስልክ እያወራ በዛው በተኛበት እሱ እራሱ ሳያውቀው ወደ ማይመለስበት አለም ተቀላቅሏል። ይህ አጋጣሚ ለመላው ቤተሰቦቹ እና ለጓደኞቹ ልብን የሚሰብር በጣም የሚያስደነግጥ እና ለማመን የሚያስቸግር አጋጣሚ ሆኗል።

ሰለሞን አፅብሃ በሀገረ አሜሪካ መኖር ከጀመረ 24 አመታትን አስቆጥሯል, መጀመሪያ በኒው ዮርክ  ከተማ አራት አመት አካባቢ ከቆየ በኋላ ያለፉትን 20 አመት በቦስተን ነበር ነዋሪነቱን ያደረገው። ሰለሞን ማለት ከህፃን እስከ አዋቂ የሚወደው፣ ከሰው ጋር ተግባቢ፣ ሃቅኛ፣ ለእውነት ሟች፣ የቤተሰቡ መከታ፣ ለሃገር ተቆርቋሪ፣ ሰው አክባሪ እና ፈርሃ እግዚአብሔር በውስጡ የተሞላ ሰው ነበር። በህይወቱ ላይ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነገር ፈርሃ እግዚአብሔር፣ የሀገር ጉዳይ እና የቤተሰብ ነገርን ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ሰው ላይ ሳይደርስ የራሱን ህይወት ቀጥ ለጥ አድርጎ መኖር ብቻ ነው የሚያስደስተው። በዚህ ጊዜ ውስጥ እህቱን እና ሁለት ልጆቹን ወደ አሜሪካ  በማምጣት እራሳቸውን ችለው ለቤተሰብም እንዲተርፉ አድርጓቸዋል, ይህ እንዲ እንዳለ እስካሁኗ ሰአት በቻለው አቅም ለቤተሰቡ እና ለጓደኞቹ ሁሌም ደራሽ ነው።

ሰለሞን አፅብሃ  በማህበራዊ ሚድያ በተለይ Paltalk  ፍትህ እና እኩልነት በአገራችን እንዲከበር ሀሳቡን በድፍረት እና በግልፅነት የሚሰጥ ወንድማችን ነበር።  ሰለሞን በፓል ቶፐክ ስሙ ሪችት ( Richit) በሚል ስም ይታወቅ ነበር፡፡

የሰለሞን አፅብሃ ልጆች ቢኒያም ሰለሞን እና ናትናኤል ሰለሞን አባታችንን እያሰባችሁ  ስለምታደርጉት የልብ ስጦታ ከልብ ልናመሰግን እንፈልጋለን፡፡ አንድ በመሆን አባታችንን እያሰባችሁ ያላችሁን ፍቅር እና አክብሮት  በመግለፅ ለእያንዳንዱ ለምታደርጉት ነገር እግዚአብሔር ያክብርልን።

ፈጣሪ እግዚአብሔር ሁላችሁንም ባላችሁበት ይጠብቃችሁ!!!

ልጆቹ : ቢኒያም ሰለሞን እና ናትናኤል ሰለሞን

https://www.gofundme.com/f/v5awm-funeral-for-selmon-atsbha?fbclid=IwAR16xlciXC3_ns8QCVXbgDNYm0BBGoYqeVowDPsXklNjzgDmJPR4tnTN2BE

Thank you,

Abby